**የሰሜን ተራሮች ጭላዳ ጥናታዊ ጽሁፍ ፕሮጀክት**

የሰሜን ተራሮች ጥናታዊ ጽሁፍ ፕሮጀክት አሁኑ ወቅት እየሰራ የሚገኘው በሁሉም ሰራተኞቻችን፣ አጥኝዎቻችን እና የአካባቢ ተባባሪዎች በሚደረገው የሚሰራ የረጅም ጊዜ ጥናታዊ ጽሁፍ ሳይት ነው፡፡ እዚህ ላይ የምንገኘው ሁላችንም የጋራ የሆነ ፍላጎት ስላለን ነው፡፡ ይህም በሰሜን ተራሮች የሚኖሩት ጭላደዎች ባህሪይ ማጥናት ነው፡፡ ይህ የመስክ ሳይት ከተለያየ ስፍራ የመጡ ሰዎች የሚሰሩበትና አንድ ላይ በቅርበት የሚሰሩበት የስራ ቦታ ነው፡፡ እርስ በርሳችን ለመከባበር እና አንደኛችን የሌላኛችንን ደህንነት የመጠበቅ ኃላፊነት አለብን፡፡ የመስክ ቡድኑ የሚወክለው ፕሮጀክቱን፣ የተለያዩ የኒቨርቲዎችን እና የዚህን ፕሮጀክት ዳይክተሮችን ይወክላል፡፡ በመስክ እና በማህበረሰቡ ዘንድ የምናሳየው ጸባይ በእኛ ላይ ተጽእኖ ማድረግ ብቻ ሳይሆን በረጅም ጊዜ ውስጥ ደግሞ በረጅም ጊዜ በፕሮጀክቱ ላይ የለዘለቄታ የሚቆይ ውጤት አለው፡፡

የመስክ ሳይቱ ከተለያዩ የህይወት አቅጣጫ ባህል እና እሴት የመጡ ሰዎች የሚሰሩበት የስራ ቦታ ስለሆነ በግለሰቦች መካል ያለውን ልዩነት መረዳትና ለመናገር ወይም ለማድረግ ተገቢ የሆነ እና ተገቢ ያልሆነ ድርጊትን መረዳት ያስፈልጋል፡፡ ይህም ማለት ማንም ሰው የትኛውንም ሰው ምቾት የሚነሳውን እና የፍርሃት ስሜት የሚፈጥርበትን ነገር ማድረግ የለበትም፡፡ እርስ በራሳችን መከባበር እና በእኩልነት መተያየት አለብን፡፡ የየግል ልዩነታችንን መከባበርና ባህልን መሰረት በማድረግ (በአመጋገብ ልማድ፣ በባህል ወይም በሀይማኖታዊ ልማዶች) በሰዎች ላይ መሳቅ የለብንም፡፡ ምክንያቱም ይህ ሰዎችን አለማክበር ስለሆነና ስራ ቦታ እንዳይገኙ ሊያደርጋቸው ስከለሚችል ነው፡፡ መስመሮችን ማክበርና በመስክ ሰይቶ ላይ ያለን ጾታ እና ኃላነት ምንም ይሁን ምን እያንዳንዳችን የየግል ቦታች የሚያስፈልገን መሆኑን መረዳት አለበን፡፡ በዚህ የመስክ ፕሮጅክት ሰዎችን ስለአካላቸው፣ ስለሚለብሱት፣ ስለወሲባዊ ባህሪያቸው ወይም ሌሎችን የግል ጉዳይ አድርገው የሚይዟቸውን ነገሮች ማውራት ተቀባይት የለውም፡፡

በተወሰኑ ጉዳዮች ላይ አንተ/አንቺ ከሌሎች ይልቅ የበለጠ ኃይለኛ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ይም እርሶን በሌሎች ዘንድ ምቾት እንዳይሰማቸው የሚያደርግ ወይም ምርጫ እደሌላቸው እንዲሰማቸው ሊያደርግ ይችላል፡፡ (አንዳንድ ጊዜ ሳያስቡት በስህተት) ከሌሎች ይልቅ የበለጠ ኃይለኛ ሊያደርጎት የሚችሉ በርካታ መንገዶች አሉ፡፡ አንዱ በይፋ በኃላፊነት ሲሾሙ ነው፡፡ ለምሳሌ በቡድን መሪነት፡፡ አንድ ሰው በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ በሚሆንበት ጊዜ ባይተዋርነት ሲሰማው ወይም በደህና ለመቆየት ሲል የእርሶን እርዳታ ሊፈልግ ይችላል፡፡ በሌላ ጉዳዮች ደግሞ በመስክ ፕሮጀክት ላይ በኃላፊነት ለሚገኝ ሰው ሪፖርት አደርግቦታለሁ ሊል ይችላል፡፡ እርሶን ምቾት የሚነሳዎት ወይም ደህንነት እንዳይሰማዎት የሚያደርግ ከሆነ በትእዛዞቻቸው መሰረት ለሰው ብለው የሚሉትን ነገር ለመስራት ግዴታ ያለቦት ሆኖ ሊሰማዎት አይገባም፡፡

የሆነ ሰው ምቾቶን ከነሳዎት ጉዳዩን ከፕሮጅት ዳይሬክተሮች መካል ለአንዱ መንገር አለቦት፡፡ አንድ ሰው የሆነ ሌላ ሰው ምቾታቸውን እንደነሳቸው ከነገሮት ድጋፍ መስጠት ይችላሉ ነገር ግን ስለጉዳዩ ለፕሮጀክት ዳይክተር መንገር የሚችሉ ወይም የማይችሉ መሆኑን ይጠይቁ፡፡ ደንቡን የመጣስ ውጤቶች ጉዳዩን በእያንደንዱ በማየት ሊፈታ ይችላል፡፡ ነገር ግን አንዳንድ

ጉዳዮች አደገኛ ሆነው ሲገኙ ከፕጀክቱ ጋር ለመስራት የተሰጣቸውን ፍቃድ መቋረጥን (ከስራ መባረርን) ሊያካትት ይችላል፡፡ የትኛውም ሪፖርት በጣም ትልቅ በጣምም ትንሽ አይደለም፡፡

ይህ የስነምግባር ደንብ የተዘጋጀው ለሁሉም የሰሜን ተራሮች  የጭላዳ ጥናታዊ ጽሁፍ ፕሮጀክት ሰራተኞችና አጥኝዎች በሰ.ተ.ብ.ፓ. እየሰሩ ሳለ  ሁላችሁም ደህንነት እንዲሰማችሁ እና  በሰላም የስራ መንፈስ እንዲኖራቸው ሳይሳቀቁ ስራቸውን እንዲሰሩ የተዘጋጀ ነው፡፡

**የካምፕ ስራ አስኪያጅ አድራሻ፡-**
**ሊዝ ባቢት፡-**lizbabbitt707@gmail.com

**የዳይሬክተሩ አድራሻ፡-**
ጃሲንታ ቢህነር – jbeehner@umich.edu
ቶር በርግማን – thore@umich.edu
ኤሚ ሉ – amy.lu@stonybrook.edu
ኖህ ስናይደር-ማክለር – nsmack@uw.edu

**የዚህ ፖሊሲ ዝርዝር ምሳሌዎች**
***የሰ.ተ.ብ.ፓ ተሳታፊዎችን ወይም በማህበረሰቡ ያሉ ሌሎችን መተቸት***

የሰ.ተ.ብ.ፓ የአካባቢ ሰራተኞችን፣ አጥኝዎችን እና የዱር እንስሳት ልማትና ጥበቃ  ኃላፊዎን በህዝብ ፊት መተቸትን በጥብቅ ይከለክላል፡፡ በተለይ በሌሎች ኢትዮጵያውያን እና ወደ ፓርኩ ለጉብኝት በመጡ ጎብኝዎች ፊት መተቸትን በጥብቅ ይከለክላል፡፡ ይህ ማህበራዊ ሚዲያንም ይጨምላል፡፡ ይህ እርሶ ያስተዋሏቸው በምግብ፣ በአለባበስ፣ በባህሪይ ወይ ሌላ አይነት ልዩነቶችን ያካትታል፡፡

***ትንኮሳ***
አንድን ሰው ያለፈላጎቱ መነካካት የሆነ ተገቢ ያልሆነ ቀልድ መቀለድ ንክኪ ማድረግ ወይም የተለየ  ባህሪ ማሳየት ነው፡፡

- *ለምሳሌ፡- አንድን ሰው ምንም ቀልድ በሌለበት ሁኔታ መምታት ወይም ተመቺው ሰው ቀልዱን እንዳልወደዱት በነገሮት ሰው ላይ ተደጋጋሚ የሆነ አካላዊ ንክኪ ማድረግ፡፡*

***አለመከባበር ወይም ከሙያ ውጪ መሆን***

በመስክ ሳይታችን ለረጂም ጊዜ ተጠጋግተው በተሰሩ ክፍሎች አብረን እየሰራን እንኖራለን፡፡ ሁልጊዜም በበሰዓቱ እና በአግባቡ መስራት አለብን፡፡ ሁሉም እቤቱ እንዳለ ያህል እንዲሰማው ማድረግ እና መቀበል አለብን፡፡ ሁልጊዜም ሙያዊ በሆነ መንገድ መንቀሳቀስ እና ባህሪያችን በመስኩ በሚኖሩ በሌሎች ህይወት ላይ እንዴት ተጽእኖ እንደሚያደርግ  ማሰብ አለብን፡፡ ሁልጊዜም

ሰው አክባሪ እና ለሌሎች የሚያስብ መሆን አለብን፡፡ለሌሎች ቦታ መስጠት እና እርሶም በሚያስፈልጎት ጊዜ ያንኑ ሌሎች እንዲያደርጉሎት መጠየቅ፡፡ ስለሚናገሩት ነገር ይጠንቀቁ፡፡ ሀሜት መርዛማ ሰለሆነ እርሶ በመስኩ ከሌሎች ጋር ያሎትን ግንኙነት እንዲሁም ሰፊውን የትምህቱን ማህበረሰብ ሊያጠፋ ይችላል፡፡ በንግግር መሃል ቸኩለው ጣልቃ በመግባት ችግሮችን አይፍጠሩ ወይም ችግሮች አሳሳቢ ጉዳዮች ከመሆናቸው በፊት ለካምፕ ስራ አስኪያጁ ያሳውቁ፡፡ የሚኖሩበት አካባቢ ጽዱ እና ለሌሎች ምሳሌ እንዲሆን ለማድረግ የድርሻዎትን ይወጡ እንዲሁም በሚችሉበት ጊዜ ሌሎን ይርዱ/ያግዙ፡፡

**ማስገደድ ወይም ጉልበተኝነት**

ሀይልን በመጠቀም ማስገደድ አንድን ሰው ያለፍላጎቱ ኃይልን በመጠቀም በማስፈራራት ፣ ለማታለል ወይም ለማስገደድ የሚያገለግል ዘዴ ነው። ይህ ወሲባዊ ሊሆን ይችላል ፣ ከእርስዎ ጋር አበረው ካልሆኑ በስተቀር ወይም ካልተኙ ደህንነታቸው ስጋት ላይ መሆኑን ማሳየት ወይም ስራቸውን እንዳያከናውኑ እርሶ የሚያውቁትን መረጃ አለመስጠት ሊሆን ይችላል፡፡

- *ለምሳሌ፡-ነባር ተማሪ ለአዲሱ ተማሪ «ዛሬ በቤቱ ውስጥ የሚገኙትን ሁሉንም ስራዎች ትሰራለህ፡፡ የማትሰራ ከሆነ ግን ለአማካሪ መምህራችን መጥፎ አጥኝ እንደሆንክ እነግዋለሁ፡፡" ማለት፡፡*

***ስነምግባር የጎደለው ወሲባዊ ተግባር***

ስነምግባር የጎደለው ወሲባዊ ተግባር ተቀባይነት የሌለው የወሲብ ዱርጊት፣ ለሰሩት ስራ ምላሽ ወሲብ እንዲፈጽሙ መጠየቅ እና ሌሎችን ወሲባዊ የሆኑ የንግግር እና ንግግር ያልሆኑ ወይም አካላዊ እንቅስቃሴን ያካትታል፡፡ ይህም አንድን የሆነን ሰው እነርሱ ሳይፈልጉ እርሶ ወሲብ ማድረግ እንደሚፈልጉ በሚጠቁም መልኩ ስለአለባበሳቸው አስተያየት መስጠትን ይጨምራል። እነዚህ ስለ አንድ ሰው ገጽታ አስተያየት ከመስጠት ተቆጥተው ወሲባዊ ግንኙነት ሊያደርጉ እንደሚፈልጉ የሚጠቁሙ አስተያየቶችን ያጠቃልላል። ይህ እንዲሁም ስለ አንድ ሰው የግንኙነት ሁኔታ ፣ ጾታዊ ዝንባሌ ወይም ወሲባዊ ልምዶች ያሉ ጥያቄዎችን ሊያካትት ይችላል።

- *ለምሳሌ፡- ወንድ የመስክ ረዳቶች ለሴት ተመራቂ ተማሪዎች ለብቻቸው በሚኖሩበት ጊዜ «ሁልጊዜም ከነጭ ሴት ጋር መተኛት እፈልግ ነበር፡፡» ሊል ይችላል፡፡*

***በፍቅር ግንኙነት መሳተፍ***

በስራ ቦታ ላይ የሚኖር የፍቅር ግንኙነቶች የስራ ቦታ አካባቢውን አሉታዊ በሆነ መልኩ ሊጎዱ ይችላሉ፤ ስለዚህም የፕሮጀክቱ ዳይክተሮች እንዲህ አይነት ግንኙነቶች እንዳይጀመሩ ይፈልጋሉ፡፡ ምናልባት ግን ከማናቸውም የመስክ ቡድን አባል ጋር እንደዚህ አይት የፍቅር ግንኙነት ካሎት ለፕሮጀክቱ ዳይሬክተር ማሳወቅ የግድ አለቦት፡፡

እባኮትን በፍቅር ግንኙነቶች መካከል የባህል ልዩነቶች እንዳሉ ይገንዘቡ፡፡ እባኮትን በሰሜን ወይም በደባርቅ ከሚገኙ አጋሮቻችን ወይ የማህበረሰቡ አባላት ጋር በማናቸውም የአጭር ጊዜ የፍቅር ግንኙነቶች ውስጥ እንዳይገቡ የምንጠይቆት መሆኑን ይገንዘቡ፡፡ ምክንያቱም ይህን ቢያደርጉ እርሶን እና በፕሮጀክቱ ያሉትን ሌሎችን በትንኮሳ አደጋ ውስጥ ስለሚጥሉ ነው፡፡ እነዚህ ግንኙነቶ ከዚህ በተጨማሪም በመስኩ ላይ ውጥረትን በመፍጠር ፕሮጀክቱን (በባለፈው ጊዜ) መጥፎ ስም ስላአሰጡት ነው፡፡

**ስለዚህ ሰነድ፡-**

ስለዚህ ይህ ፕሮጀክት ከአስር አመት በላይ ለሚሆን ጊዜ ከአካባቢ ሰራተኞች እና ከአጥኝዎች ጋር እዚህ ላይ የሰራ ቢሆንም እንኳን ፕሮጀክቱ ይህንን የመሰለ ነገር ሲሰራ ለመጀመሪያ ጊዜ ነው፡፡ አሁን ያለው ሀሳብ ከፕሮጀክቱ ጋር ግንኙነት ላላቸው ለሁሉም አጥኚዎችና ሰራተኞች ይሰጣል ብየ አስባለሁ፡፡ ስለዚህም በእንግሊዝኛ ለእንግሊዝኛ ተናጋሪዎ በአማርኛ ደግሞ ለአካባቢ አጥንዎች ይሰጣል፡፡ የዚህ ፕሮጅክት ባልደረባ ለሆናችሁት ጽሁፉን ለማንበቢያ የሚሆን ጊዜ ይሰጣቸዋል፡፡

ስለዚህ ጽሁፍ ግልጽ እንዲሆንልን ውይይት የምናደርግበት ከሁሉም አጥኝዎቻችን ጋር ስብሰባ ይኖረናል፡፡ ትልቁ የሚያሳስበን ነገር ከአካባቢ ሰራተኞቻችን መካከል ማናቸውም ስህተት የሆነ ነገር እንደሰሩ እንዲሰማቸው አንፈልግም (ምክንያቱም ይህ በባለፈው ጊዜ ተፈጥሮ ሊሆን ስለሚችለው ስላለፈው ነገር ለመውቀስ አይደለም)፡፡ ንጹህ ከሆነ ነገር መጀመር እና ይህ አዲስ ልማድ እንዲሆን እንፈልጋለን፡፡በእያንዳንዱ አመት አዳዲስ ሰዎች ወደ ስራው ሲመጡ መስራት እንፈልጋለን፡፡ በአሁኑ ሰአት የካምፕ ስራ አስኪያጃችን ይህንን ስብሰባ ይመራል፡፡ ነገር ግን ለወደፊት አመታት ፕሮጀክቱ ከቀድሞ አጥኝዎቻችን መካል አንዱን-አንዱን ኢትዮጵያዊ የመስክ ረዳት እንዲመራ ይፈልጋል፡፡ ስለዚህም የዚህ የአማርኛ ትርጉም ለወደፊት ስብሰባዎችም ሊጠቅመው ይችላል፡፡

በዚህ ወቅት ልናተኩርበት የምንፈልገው በሌሎች ሳይቶች ላይ በጣም ብዙ የወኖ የትንኮሳ ጉዳዮች የነበሩ ሲሆን በዚህ ሳይት ላይ ግን እንደዚህ አይት ነገር እንዳይፈጠር በማድግ ይህንን የስራ ቦታ የተሸለ የስራ ቦታ ለማድረግ ይህንን የስነምግባር ደንብ መተግበር እንፈልጋለን፡፡ ለአሁኑ የቃል ስምምነት ነው፡፡ ዳይክተሮች ማንንም እንዲፈርምበት አይፈልጉም (ይህም በእርግጥ ደባሪ ነገር ነው ብየ አስባለሁ)፡፡ነገር ግን ለዚህ ስብሰባ ዋናው ነጥብ የመስክ ሳይታችንን አጠቃላይ መፈክር ለማሳየትና ዝርዝር ትርጉሞችን እና የተሳሳቱ ድርጊቶች እንዴት ስህተት እንደሚሆኑ ምሳሌ ለመጥቀስ ነው፡፡ በተጨማሪም በአሁኑ ሰነድ ላይ ማናቸውም ግብረ መልስ ቢኖሮት የምቀበል መሆኔን መግለጽ እፈልጋለሁ፡፡ ሁሉም የአካባቢ የመስክ ረዳቶቻችን ወንዶች ናቸው፤ስሜታቸውን ወይም ፍላጎታቸውን ለመጫን አንፈልግም ነገር ግን ከዚህ ጎን ለጎን በእኩል ወሲባዊ ትንኮሳን በተመለከተ ምንም አይነት የመቻቻል ፖሊሲ የለንም፡፡ ዳይክተሮች እያንዳንዱን ሪፖርት በእያንዳንዱ ጉዳይ የሚያዩት ይሆናል፡፡ ይህ ሰነድ ማናቸውም አጥኝዎች ስራቸውን ሲሰሩ ሳላ ማናቸውም ነገር ቢፈጠር እንዴት ሪፖርት እንደሚያደርጉ ስለሚያተኩር ለሁሉም ጥሩ ይሆናል፡፡ እውነት ለመናገር በእርሶና በእኔ መካከል ስላለው ነገር ስናገር-የእኛ በአንፃራዊነት ደህንነቱ የተጠበቀ የመስክ ሳይት ሲሆን ሰራተኞቻችን ደግሞ የእውነት አስተዋዮችና/አስደናቂ ባህሪይ ያላቸው ናቸው፡፡ በአብዛኛው ችግር የሚፈጥሩት ከአሜሪካ የመጡ ተመራቂ ተማሪዎች ረዳቶች ናቸው-ስለዚህ ይህ ሰነድ የአካባቢ ረዳቶችን እንዲያግዛቸው

እወዳለሁ፡፡ መጥፎ በሚሰሩ ሰዎች ሲቸገሩ ድምጽ እንደሌላቸው/ድምጻቸውን ማሰማት የማይችሉ እንደሆኑ ሊሰማቸው አይገባም፡፡

እባኮትን ፕሮጀክቱ ምን ያህል እንዲከፍል እንደሚፈልጉ ልወቀው!:-)

ስዚህ ሰነድ ማናቸውም ጥያቄ ካሎት ያሳውቁኝ!

ከሰላምታ ጋር፣
ሻርሚ
--
ሻርሚ ሰን
እጩ ዶክተር
የአንትሮፖሎጂ ትምህርት ክፍል
ሚችጋን ዩኒቨርሲቲ
የሰሜን ተራሮች ጭላዳ የጥናታዊ ጽሁፍ ፕሮጀክት
ጽ/ቤጽ፡- 4058 ኢስት ሆል